# እኛም አለን ሙዚቃ...
# እኛም አለን ቅኔ

-በአበራ ለማ

የሙዚቃው ደራሲና አቀነባባሪ ሊቀ መኳስ ዘነበ በቀለ ከሚኖሩበት ከእስቶክሆልም ከተማ ያስተላለፉልኝ የግብዣ ጥሪ፣ ወዲያ ወደሳቸው አገር እንዳመራ ሰበብ ሆኖኝ ሰነበተ። ሊቀ መኳስ ዘነበ፤ "በስዊድን የኢትዮጵያ ሙዚቃና ድራማ የምርምር ማእከል" ሊቀ መንበር ናቸው። ባስተላለፉልኝ ጥሪ ላይ "ኖቬምበር 28 ቀን 2009 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ሙዚቃ በኖታ የተሰራበት ኮንሠርት ምረቃና "በረከተ መርገም" በመባል የሚታወቀው የባለቅኔ ኃይሉ ገብረ ዮሃንስ (ገሞራው) ሥራ 40ኛ ዓመት መታሰቢያ በዓል ላይ ይገኙልን..." የሚል ዐቢይ ሃረግ ይገኝበት ነበር። እናም በስፍራው ተገኝቼ ለዛ የነበረውን የጥበብ ምሽት ታድሜበታለሁ። በእለቱ አመሻሽ ላይ በተጀመረውና እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ በዘለቀው በዚህ ልዩ ዝግጅት ላይ፣ በስዊድን ነዋሪ ከሆኑ ኢትዮጵያውያንና የስዊድን ዜጎች በተጨማሪ፤ ከተለያዩ አገሮች የመጡ ተጋባዥ እንግዶች ጭምር ተገኝተውበታል።



ሊቀ መኳስ ዘነበ በሥራ ላይ

ሮግስቬድ በሚባለው ትልቅ አዳራሽ ውስጥ በተካሄደው በዚህ ባይነቱ ልዩ በሆነ ዝግጅት የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት ላይ፤ የእለቱ ዝርዝር መርሃ ግብር በገጣሚ ማቲያስ ማርቆስ (በጫካ ስሙ ወለላዬ) ቀርቧል። በመርሃ ግብሩም መሠረት፣ የማእከሉ ሊቀመንበር ሊቀ መኳስ ዘነበ፣ ባለ ላንቃ ውብ ካባቸውን ደርበው፣ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር አድርገዋል። በንግግራቸውም ላይ የማእከሉን ሥልጠና ለመውሰድ በተሰባሰቡ ፈቃደኛ ያገር ልጆች ብርቱ ጥረት ህልማቸው እውን ሊሆን መቻሉን ኣስታውቀዋል። የኢትዮጵያን ባህላዊ የሙዚቃ ቅኝት በዘመናዊው የሙዚቃ ቅማሬ (ኖታ) ጽፎ፣ ከዚያም ያንን ኖታ እያነበቡ፤ ትዝታን፣ አምባሰልን፣ አንቺሆዬ ለኔንና ባቲን የመጫወትን ፈተና የማለፍን ብርታት ይጠይቅ እንደነበርም፣ መምህርም ጭምር የሆኑት ዘነበ አስታውቀዋል። የወደፊት ትልማቸውም፣ የስዊድንን ድንበር



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ተሻግረው በኖርዌይ፣ በፊንላንድ፣ በዴንማርክና ዘልቀውም በቀሩት ያውሮፓ አገሮች ይህን ልዩ ኮንሰርታቸውን ለሕዝብ ለማቅረብ ማቀዳቸውን ገልጠዋል።

በወጣው መርሃ ግብር መሠረት የሙዚቃው ድግስ መቅረብ ጀምሮ፤ በክፍል አንድ ዝግጅት ውስጥ የተካተቱት፣ "የኩበቱ ጭስ(በህብረት)፥ የማታ ዝምበር(ሶሎ በሰሙ)፥ የተበተነ ዘር(በሰብለ)፥ አዳሽረጪ(በማርሽት)፥ እህህ…(በፋሲል)፥ ኢትዮ ኦፐሬታ(በቀድሞው ዲፕሎማት በአቶ ንጉሡ ታምራት ይገዙ)፥ የክላርኔት ጨዋታ (Mozart's Die Wiener Sonatinnen እና አምባሰል በሊቀ መኳስ ዘነበ)፥ ዘለሰኛ በዣን ሥዩም ሄኖክና የእረኛው ዋሽንት በህብረት ቀርበዋል።

ይህ በዘመናዊ የኖታ ቅማሬ ተቀነባብሮ የቀረበው ያገርኛ ሙዚቃ፣ ያድማጭን ስሜት ሰቅዞ ይዞ ታሉበት የሚያወዛውዝ አንዳች ምትሃታዊ ዓይነት ኃይል የነበረው ነው። ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያን የታጠቀው አርኬስትራ፤ በሊቀመኳስ ዘነበ አቀናባሪነት (composer) እየታገዘና እየተመራ ሁላችንንም አሸንፎ አስመሽቶናል። ለካስ የሙዚቃ ጥበባችን እንዲህም ረቆና ሽግኖ ሊቀርብ ይችላልና እያልን ለመንፈሳችን ሀሴትን መግበንበታል። እያንዳንዱ የሙዚቃ መሣሪያ ቅኝት እሰሌዳው ላይ ባለው ኖታ እየተኳሸ፤ በሙዚቃ ቅንብሩ መሪ እንቅስቃሴ ሲለካ፤ ሩሃችን በደስታ መስረቅረቋን የምንረዳው ከየሰመመናችን ድንገት ስንናጠብ ብቻ ነበር። በተጓዳኙም እንደ ዣን ሥዩም ሄኖክ ("ዣን ሥዩም" የማእርግ ስሙ መሆኑን ልብ ይሏል) የመሰለ ድምጻዊ ትንግርት የሚያስብል ፈጠራውን ባስረቅራቂው ድምጹ አስደምጦናል። ዣን ሥዩም ካገርኛው አለባበሱ አንስቶ፣ እስከ ለየት ያለው ዜማውና ጥልቅ ያገጣጠም ስልቱ ድረስ ለብቻው ሊጠናና ብዙ ሊባልለት የሚገባ የፈጠራ ሰው ነው። ስዊድን ውስጥ፣ ባጭር ጊዜ ቆይታዬና ትውውቄ ሳልጠግባቸው ከተለየኋቸው ብርቅዬ የጥበብ ሰዎቻችን አንዱ ነው። በጣም ብዙ ብዙዎችም ቀርተውብኛል…



ዣን ሥዩም ሄኖክ

ገጣሚ መስከረም አየለ (ወይንም በጨካ ስሟ "ማራኪ") እንደ ምግባረ ቀናው ማቲያስ ሁሉ፣ ለምሽቱ ዝግጅት ቅመም ሁና ያመሸች ትጉህ እህት ነበረች። ቀደም ብላ የሊቀ መኳስ ዘነበን ማንነት ከስር ከመሠረቱ እያነሳች ለታዳሚው እንዳስተዋወቀችው ሁሉ፤ የሙዚቃውን ንጉሥ ዶ/ር ጥላሁንን ያዘከረችበት እጥር ምጥን ያለ ግጥሟን አስደምጣናለች። መስከረም ሁለገብ ባለሙያ በመሆኗም ታድላ ኑራ፣ እግር በግር እየተከታተለች የጋሼ ኃይሉንም የኔንም በንተሱ (profile) ለውቂያ ለማብቃት ብዙ መድከሟን ልብ ብለናል። በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የሙዚቃው ድግስ አልፎ አልፎ ላይነት ጣል እየተደረገ ምሽቱን እያዋዛ ይዞን እንዲነጉድ መዘየዱ፣ ያቀራረብ ብልሃታቸውን ልቀት የሚያሳይ ነበር።

በሁለተኛው ክፍል ዝግጅት ላይ የሙዚቃ ጓዱ በሕብረት ያቀረባቸው ውብ ዝማሬዎች፣ የአእዋፍትን የምሽትና የማታ ሕብረ ዝማሬን የሚያስታውሰን ነበር። ወጣቶቹ ሥልጡን የኖታ ሙዚቃ ቀማሪዎች ሊቀ መኳስ ዘነበን እየተከተሉ፣ በጣቶቻቸው የሙዚቃውን መሣሪያ ሲያናግሩ፣ በድምጻቸው ደሞ ሰፈውን አዳራሽ ይሞሉት ነበር። "እኛም አለን ሙዚቃ፥ ተማሪ ነኝ፥ አዳራሹ ቤቴ፥ አልመጣም ቀረሁ፥ ያ ለሰለሴ ቢራቴ፥ ወይ ካሊብሶ፥ የሚያስለቅስ ፍቅር፥ በጊዜው አልፈርድምና አዲስ ፍቅር" የተሰኙት ነባር አገርኛ ጨዋታዎች በህብረት ተደምጠዋል። ግሩም የተዋጣላቸው የሥራ ፍሬዎች ነበሩ።

በእንግሊዝ አገር ተቀማጭ የሆነችውና ባገር ጉዳይ ላይ አፍቃሬ ጭውውት የሆነችው ፍሬ ሕይወት ተሰማ እሸቴ (በፍሬ ሕይወት አዲስነት በብርቱ እምትታወቀው) የዚህ ታላቅ የጥበብ አዝመራ በዓል አንደኛ ታዳሚ ነበረች። ፍሬ ሕይወት ላዘጋጆቹ ያላትን አክብሮትና አድናቆት ከማስደመሟም በላይ፣ ጋሼ ሃይሉን በልዩ ሽልማት አድምቃዋለች። (አንተ የምለው በቅርበቴ እንጂ በምንም በምንም ታክዬው እንዳልሆነ ይጤንልኝ) የኢትዮጵያ ባንዲራ ከነሞዓ አንበሳው ምስል ያለበት ትልቅ የወርቅ ቀለበት በእውቅ አሠርታ፣ ለዚህ ዘመን ለማይሽረው ታላቅ ባለቅኔያችን ሸልማዋለች። ይቺ ያገር ጉዳይና ፋይዳ ወዳለበት ሰፍራ ሁሉ እየተጓጓዘች፣ ለወገንና ላገር ያላትን ጥልቅ ፍቅሯን የምትገልጽ እህት፣ ውስጣዊ ብርታቷና ንቃቷ ድንቅ የሚሰኝ ነው።

ከሙዚቀኞቹ አንዱ የሆነው አርቲስት ፋሲል በቀለ የገሞራውን "በረከተ መርገም" አሳምሮ ከቀራልን በኋላ፤ ጉዟችን ወደ ጋሼ ኃይሉ ለመድረስ እየተቃረብን እንደሁ ጠቋሚ ነበር። ወዳጃችን ገጣሚ ማቲያስ "ጋሼ ኃይሉን አገኘሁት" በሚል ርእስ ከጥቂት ዓመታት በፊት አንጉቶት የነበረው የግጥም ትሩፋቱን ተደረሰን። ይህንን ብርቅዬ (legendary) ሰዋችንን እንደምን አክብደና አክብሮ ያየበትን የገጣሚ ምናቡን አልሰወረንም። ተከትሎም በምድብ ሦስት ላይ ከተመለከተው የሙዚቃ ድግስ ውስጥ በጃን ሥዩም ሄኖክ መሪነት "የቡሄ ሶለላ" በህብረት ተጨወተ። እናም ወደ ጋሼያችን በደምብ ተጠጋን...

የቀድሞው የቀ.ኃ.ሥ. መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም (ኮተቤ) የሙዚቃ መምህር የነበሩትና፣ በኋላም ለከፍተኛ የሙዚቃ ትምህርት ወደ ቀድሞዪቱ ሶቭዬት ህብረት ተልከው የማስትሬት ድግሪያቸውን ያገኙት ሊቀ መኳስ ዘነበ፤ ከአርባ ዓመታት በፊት በዚሁ በመምህራን ማሰልጠኛው ተቋም የሥራ ባልደረባቸው የነበሩትን ዝነኛውን እምቢ ባይ ባለቅኔ ሃይሉ ገሞራውን ተዝቆ ከማያልቀው ትዝታቸው ቀንጠር አድርገው ለታዳሚው አስተዋውቀዋል። ከብዙ በጥቂቱም እንዲህ አሉን... ያኔ ከጋሼ ኃይሉ ጋር ኮተቤ አስተማሪ ሳሉ፣ አንድ ቀን የቅርብ አለቃቸው የነበሩት ዶ/ር ልዑል ሰገድ ዓለማየሁ አርፍዶ ወደ ሥራው ሲገባ ያገኙትን ጋሼ ኃይሉን ይፈታተኑታል።

*"ለምንድነው የምታረፍደው? እንዲህ የምታረፍድ ከሆነ ከደሞዝህ ነው የምቆርጥብህ!..."*
ይሉታል።
*"መጀመሪያ ካንተ ደሞዝ ላይ ቁረጥና..." ይመልሳል ጋሼ ኃይሉ።*
*"ለምን ከኔ ደሞዝ?"* ይጠይቃሉ ዶ/ር ልዑል ሰገድ።
*"ካለ ዛሬ በስተቀር ሥራህን ሠርተህ ስለምታውቅ፣ የዛሬ ደሞዝህ ብቻ ሲቀር የቀረውን ሁሉ ቆርጠህ ናና፣ ተዚያ በኋላ የኔን ትቆርጣለህ..."* ብሎ አሳፈራቸው ሲሉ፣ ለሞገደኝነታቸውና ለእምቢ ባይነታቸው ያይን ምስክርነታቸውን ሰጥውታል።

ጋሼ ሃይሉ በተያዘለት የመድረክ ሰ(ሰ)ዓት መሠረት እታዳሚው ፊት ብቅ አለ። አዳራሹ በሆታ፥ በእልልታና በጭብጨባ ጋዬ። የታሪከኛውን የ"በረከተ መርገም"ን የ42 ዓመታት


PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የትግል ጉዞ ከተለያዩ ገጠመኞቹ ጋር አዋውቶ በሰፊው አጫወተን። በቀድሞው የቀ.ኃ.ሥ. ዩኒቨርስቲ የጉባዔ አዳራሽ ውስጥ ይህን በምጸትና በአያዎ ዘይቤ በጅጉ የተኳሸ ሥራውን ካቀረበ ወዲህ፣ ኑሮው በእስርና በስደት ዓለም ውስጥ የተቀነበበ ሁኖ፣ ሰባት አሠርቱን ሊያስቆጥር ተዋዝሟል። ውድ እናት አገሩን እንደናፈቀ፥ የቢረቀበትንና የዘለለበትን የእስጢፋኖስ አምባ ልጅነቱን በትዝታ መረብ እንዳጠመደ አለው። እምድረ ስዊድን ላይ ሁኖ የሚያገሳው የጠቢያ አንበሳ ገሞራው፣ ስምን ግብር እምደሚያወጣው ታረጋገጠልን እነሆ ትውልድ አልፎ ሌላ ትውልድ ተተካ። ግና ጋሼ ዛሬም ብርቱ ነው... ተመስገን።



እውቁ ባለቅኔ ኃይሉ ገብረ ዮሃንስ (ገሞራው)

ጋሼ ኃይሉ፣ በምሽቱ “የጎዳና ቅኔ” ብሎ ያቀረበው አንድ ጥንታዊ የግእዝ ቅኔ የራሱ አፈጣጠርና ያመጣጥ ሰብበ እንዳለው አልሸሸገንም። ይህ በግእዝ ቅኔ ቤት ታላቅ ዋጋ የሚሰጠው “የጎዳና ቅኔ”፣ ያንድ ደበሎ ለባሽ የቆሎ ተማሪ ያይምሮ ንቃት ውጤት እንደሁ አስተዋውቆናል። የቆሎው ተማሪ ከመንደር መንደር ለቀፈፋ ሲዞር ከውሾች ጋር ክፉኛ እየተጣላ፣ እግረ መንገዱን የተቀኘው ድንቅ ቅኔው እንደሁ አውስቶናል። ጋሼ ኃይሉ ያንን ቅኔ እመድረክ ላይ ወጥቶ በተቀኘበት (resite) ወቅት፣ ያዳራሹ ጸጥታ ግብዓት፣ መርፌ እንኳን ቢወድቅ ኮሽታው እንዲሰማ ያህል ነበር። የድምጹ ግርማ ሞገስና የቅኔው አደራደር ይትብሃል ግዘፍ ነስቶ ሁላችንንም ትንፋሽ ያስዋጠ ነበር። በዚህም የጋሼ ኃይሉን ታላቅ ሰብእና ከነሙሉ ክብሩና ጥልቅ እውቀቱ ጋር በጉልህ ለማየት አስችሎናል። በሕይወት ከተረፉን ጥቂት ብርቆቻችን አንዱ በመሆኑ፣ ልንከባከበው ልንሳሳለት የሚገባ ያገር፥ የባንዲራ፥ የታሪክ፥ የባህል ተምሳሌት ቅርሳችን ነው።

ጋሼ ኃይሉ በክብር እንግድነት ያልተጋበዘበት የሚሊኒዩም ዓይነት ክብረ በዓል ከቶም ከቶም ምሉእ ሊሆን እንደማይችል ምስጢሩ ገና ያልተገለጠላቸው “ጨዋዎች” የመኖራቸው ጉዳይ ሲያስገርመን መኖሩ እንዳይላመደን እንፈራለን። ስለዚህም ነው፣ ይህ የኢትዮጵያ ሙዚቃና ድራማ የምርምር ማእከል፣ ለጋሼያችን ክብር ሰጥቶ በዚህ ምሽት እንድናከብረው በማድረጉ ምስጋናን የሚቸረው። ማእከሉ በተቋቋመበት ዓላማ መሠረት ያፈራውን ጣፋጭ ፍሬውን ከማቅመሱም ባሻገር፣ ገሞራውን የመሰለ ያገር አድባር በማስተገኑ ብርታትና ትጋትን ያልተመኘለት ታዳሚ አልነበረም።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ለወደፊቱም ተመሳሳዩን መርሃ ግብር እያወጣ፣ በሌሎችም ያውሮፓ አገሮች ጭምር እየተንቀሳቀሰ፣ ይህን መልካም ፍሬውን ለሌሎች ሁሉ እንዲያቃምስ ምኞቴ ነው። አገራዊ ጥበብ ባገር ጥበበኞች እንዲህ ጣፍጦና ሸግኖ ሲቀርብ፣ ከገበታው ለመቅመስ የማይታደም የለምና መበርታት ነው።

(ረቡዕ፥ ሕዳር 23 ቀን 2002 ዓ.ም.)



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com